1. ጌታችንና ኢየሱስ ክርስቶስ ወደጌርጌሴኖን በሄደ ጊዜ ከተከሰቱት ነገሮች ውስጥ የማይመደበው የትኛው ነው?
ሀ) ጌታችን በሰዎቹ ላይ አድረው የነበሩትን አጋንንት ወደ እሪያዎቹ ሰደዳቸው
ለ) በከተማዋ ያሉት ሁሉ ጌታችንን ሊቀበሉት ወጡ
ሐ) እሪያዎቹ አጋንንቱ ባደሩባቸው ጊዜ ከአፋፉ እየሮጡ ወደ ባሕር ውስጥ ወድቀው ሞቱ
መ) በከተማዋ ያሉት ሰዎች ጌታችንን ሲያዩት ከሀገራቸው እንዲሄድ ለመኑት
ሠ) መልስ የለም

2. በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ላይ ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት ምን ያህል ዓመት ነው ደም የፈሰሳት?
ሀ) 12 ለ) 6 ሐ)7 መ)13

3. ጌታችን ያበረከተው አምስት እንጀራ እና ሁለት ዓሳ ስንት መሶብ ተረፈው?
ሀ)9
ለ)11
ሐ)12
መ)15

4. ጌታችን ለስንት ሰዎች አምስት እንጀራ እና ሁለት ዓሳ መገበ?
ሀ)ሴቶች እና ህፃናት ሳይጨመሩ አምስት ሺህ
ለ) ሴቶች እና ህፃናት ጨምሮ አምስት ሺህ
ሐ) አምስት ሺህ ሴቶችን እና ሕፃናት
መ) መልስ አልተሰጠም

5. ጌታችን በጌርጌሴኖን ከሰው ወደዕሪያዎች መንጋ ያባረራቸው ርኩሳን መናፍስት ስም ማን ነበር?
ሀ) ሌጌዎን ለ) ብዔል ዜቡል ሐ) ዲያብሎስ መ) ኢጋንንት

6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያ ጋኔን የወጣለትን ሰው ምን እንዲያደርግ መከረው?
ሀ) ወደ ቤቱ እና ወገኖቹ እንዲሄድ
ለ) እንዲከተለው እና ደቀመዝሙሩ እንዲሆን
ሐ) እግዚአብሔር ስላደረገለት ታላቅ ነገር ስለይቅርታውም እንዲናገር
መ) ሀ እና ሐ

7. "ከማይቀበላችሁ ቃላችሁንም ከማይሰማችሁ ግን ከዚያች ቤት ወይም ከዚያች ከተማ ወጥታችሁ የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ" ሲል
ሀ) ትቢያው ከእኛ እንደተለየ እናንተም ከእኛ ልዩ ናችሁ ለማለት
ለ) ትቢያው እንደረገፈ እናንተም በሲጋችሁ መቅሰፍት በነፍሳችሁ በገሃነም ትጠፋላችሁ ለማለት
ሐ) እኛ ሰው ከተፈጠረበት አፈር አልተፈጠርንም ለማለት
መ) ሀ እና ለ

8. ሌጌዎን ያደረበትን በሽተኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየት አዳነው?
ሀ) በጌርጌሴኖን
ለ)በኢየሩሳሌም
ሐ)በቃና ዘገሊላ
መ) በናዝሬት

9. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌጌዎን የተባሉትን ጋኔን ወዴት እንዲሄዱ ፈቀደላቸው?
ሀ)ወደ ተራራ ጫፍ
ለ)ወደ ሲኦል
ሐ)ወደ ዕሪያ መንጋ
መ)ወደ ጥልቅ ባሕር

10.ለዐሥራ ሁለት ዓመት ደም የፈሰሳት ሴት እንዴት ዳነች?
ሀ)ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጁን ጭኖባት
ለ) የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ልብስ ነክታ
ሐ) በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይል እና በእርሷ እምነት
መ)ለ እና ሐ

11. ጣሊታ(ጣቢታ) ማለት ምን ማለት ነው?
ሀ)አንተ ጎበዝ
ለ)አንቺ ብላቴና
ሐ) አንተ ሰነፍ
መ) አንቺ ጻድቅ

12.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የኢያኢሮስን ልጅ ሲያድን በቤቱ ውስጥ ስንት ሰዎች ነበሩ?
ሀ)4 ለ)5 ሐ)6 መ)7

13.የኢያኢሮስን ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ካስነሳት በኋላ ምን እንዲያረጉ አዘዘ?
ሀ) የተደረገላቸውን ለሁሉም እንዲናገሩ
ለ)የተደረገላቸውን ለማንም እንዳይነግሩ
ሐ) ምትበላውን እንዲሰጡአት
መ) ለ እና ሐ

14.በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሀገሩ ተብላ የተጠቀሰችው ከተማ ማን ናት?
ሀ)ናዝሬት
ለ)ኢየሩሳሌም
ሐ)ቁስጥንጥንያ
መ)ሮም

15.ንጉሥ ሄሮድስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው ብሎ ያስብ ነበር?
ሀ)ኤልያስ
ለ)ሙሴ
ሐ)መጥምቁ ዮሐንስ
መ)ሁሉም

16.ጌታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ስንት ስንት አርነ ላካቸው?
ሀ) አራት አራት
ለ) ሶስት ሶስት
ሐ)ሁለት ሁለት
መ)ለየብቻ

17.መጥምቁ ዮሐንስ ንጉሥ ሄሮድስን ስለምን ገሰጸው?
ሀ)የወንድሙን ሚስት ስላገባ
ለ)ዮሐንስን ስላሰረው
ሐ)ሕዝቡን በአግባቡ ስላላስተዳደረ
መ)ሁሉም

18.ስለመጥምቁ ዮሐንስ ሞት ትክክል የሆነው የቱ ነው?
ሀ) ንጉሥ ሄሮድስ በእርሱ ላይ ያምጽበት ስለነበር ተናዶ አስገደለው
ለ) ሄሮድያዳ ጠልታው ነበርና ሄዳ አንገቱን አስቆረጠችው
ሐ) የሄሮድያዳ ልጅ የእናቷን ምክር ሰምታ ንጉሡን የዮሐንስን አንገት ቆርጦ እንዲሰጣት ጠየቀችው
መ) ለ እና ሐ

19.ከሚከተሉት ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምዕራፍ 5 ላይ ካደረጋቸው ተአምራት ውስጥ አይካተትም?
ሀ) ሌጌዎን ያደረበትን በሽተኛ መፈወሱ
ለ) ጣቢታን ከሞት መስነሳቱ
ሐ) ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም የፈሰሳት ሴት መፈወሷ
መ) በባሕር ላይ መሄዱ

20. በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ ደቀመዛሙርቱ የነበሩበት ታንኳ ሲናወጥ ጌታ ወዴት ነበር?
ሀ) ሕዝቡን ሊያሰናብት
ለ) ተኝቶ
ሐ) ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጥቶ
መ) ሀ እና ሐ
ሠ) ሁሉም